# መለኮታዊ ዝማሬ

ሰለሞን ሽፈራው

ለተቀደሰ ተልዕኮ፣ ባሰመርከው ቅዱስ መንገድ
መስቀልህን ተሸክመህ፣ ወደፊት ስትራማመድ
አበክረህ የቆምክበት፣ የተልዕኮህ ንፍቀ ክበብ
ራዕይህ ድንበር የለሽ፣ በዘመን የማይገደብ
መሆኑን ስትገነዘብ፣
ምንተ ህያው ሀገር ወገን፣ በአንክሮ ልትጠበብ
መስቀልህን ተሸክመህ፣ ጎለጎታን ስትወጣ
ይህ ዓለም በክፉት እጁ፣ ጠልፎ ሊጥልህ ቢቃጣ
ደጋግሞ ቢፈታተንህ፣ የመናፍቃን ውኸንብር
በኢያጎ መሰሪነት፣ እምነትህን ሊጎደፍር
ወዳጅ ዘመድ ተመስሎ፣ መቃብርህን ሲቆፍር
ከግራ ቀኝ ያንተን ውድቀት፣ ሲያውጠነጥን
ውሎ ቢያድር፣
ለተልዕኮህ ታመን እንጂ፣ በፍፁም እንዳትደነብር…!
ሰው ለተልዕኮው ሲታመን፣ ባመነበት ፀንቶ ሲኖር
ሌሎች ሊገድሉት አይችሉም፣ ካልሞተላቸው በስተቀር!
ሲል ይሰማኛል ዘወትር፣

መለኮት የህያው ፍቅር፣
በረከቱን ሊያሰርፅብኝ፣ በልቤ ውስጥ ሲዘምር።
ሰሊጡን ከኑግ እማይለይ
የኦሪት ዘመን መታበይ
ባላጎበጠው ልቦና
ጥላቻ በማያዝለው፣ የፍቅር እግረ-ህሊና
መስቀልህን ተሸክመህ፣ ጎለጎታ ስታቀና
አርቀህ በምታልመው፣ የህያውነት ተራራ
ለተከታታይ ትውልዶች፣ እንደፀሐይ ልታበራ
ተልዕኮህን ዳር ለማድረስ፣ ወደግብህ ስታመራ
ይህ ዓለም በክፋት እጁ፣ ቢያዋክብህ ከቀኝ ግራ…
ደጋግሞ ቢፈታተንህ፣ የመናፍቃን ውኸንብር
በኢያጎ መሰሪነት፣ ጠልፎ ሊጥልህ ቢሞክር
የኦሪት ዘመን መታበይ፣ ባመነቸከው መቅበዝበዝ
ምናልባት የዳግም ልደት፣ ድምቀትህን ለማደብዘዝ
በኢያጎ መሰሪነት፣ ያንተን ተልዕኮ ሊመርዝ
ከየአቅጣጫው የሚታለም፣ የሺህ ክፋት ሺህ
አፈ ሙዝ…

አናትህ ላይ ቢነጣጠር፣
የጥይት ዶፉ ቢዘንብብህ፣ ደረትህ መሀል ቢቆጠር
ለህሊናህ ታመን እንጂ፣ በፍፁም እንዳትሸበር…!

ሰው ለህሊናው ሲታመን፣ ባመነበት ፀንቶ ሲኖር

ጠላቶቹ አይገድሉትም፣ ካልሞተላቸው በስተቀር።

ሲል ይሰማኛል ዘወትር፣

መለኮት የነፍሴ አለኝታ፣

ይህ ዓለም በውኸ'ንብሩ፣ አድክሞኝ እንዳልፈታ

ተልዕኮየን ሲባርከው፣ በህያው ቃሉ ሹክሹክታ።